# በ ” ሰሞኑ የተስፈኞች ጫጫታና እንድምታው " ላይ የቀረበ አስተያየት

በ “ የሰሞኑ የተስፈኞች ጫጫታና እንድምታው " ርዕስ ከዶክተር አሸናፊ ጎሣዬ በሚል የተጻፈውን አጭር ጦማር አንብቤ በቀረቡት ጉዳዮችና እንድምታቸው በተሰኘው ላይ ስለተገረምኩ ይህን አጭር ምላሽ መስጠት ተገቢ መስሎኝ አቅርቢያለሁ :- የጦርነት ፊሽካ ከነፋት ጀምሮ በስም በመኖራቸው ብቻ ድልን እንደመና ካልታወቀ ምንጭ እንዲወርድላቸው ተስፋ እስከሚያደርጉት ድረስ ያሉትን የፖሊቲካ ድርጅቶች በማነጻጸርና ጠባዮቻቸውን በአራት በመከፈል ተንትነዋቸዋል፤ የድርጅቶቱ ጠባይ ከዚህም በላይ ባለ ቁጥር ሊገለጽ ይችላል። ይኸውም በአጭሩተመሣሣይ ዓላማ እንኳ እየተናገሩ በተግባር እርስበርሳቸውም የሚቃረኑ ድርጅቶች እንዳሉ ለሁሉም ግልጽ ነው። የነሱን ትንተና በተሻለ ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ብዙዎች ከጻፏቸው ውስጥ አሁን በእሥር ላይ ያለው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ እና ፕሮፌሰር መስፍን የጻፏቸውን በማንበብ የበለጠ መረዳት ይቻላል።

ዶክተር አሸናፊ እንዳስቀመጡት የጦርነት ፊሽካ ስለሚነፉት፣ድብቅ ዓላማ ይዘው የተለያዩ ጭንብሎችን ያጠለቁ የሚሏቸውን፤ በምንም ይሁን ማንም ይምጣ ወያኔ ብቻ ይወገድ የሚሉትን፤ ድሮ በተፈጸሙ ጥፋቶች ይቅርታ በመባባል ለጋራ ዓላማ እንታገል የሚሉትንና ካለኛ አመራር ሕዝባዊ ትግል ውጤት አይኖረውም ከሚሉትም አንጻር አሁንም የብሔር-ብሔረሰብ ጭንብል አጥልቀው ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት እንታገላለን በሚሉት ላይ አተኮራለሁ።

ድብቅ ዓላማ ይዞ ሕዝቦቻችንን ሲያፋጅና መለያየትን በመጠቀም በአገራችን ላይ ሙሉ ሥልጣን ይዞ የተደበቀ ዓላማውን ለሩብ ምእተ ዓመታት ይዞ ሕዝቦቻችንን አታሎ በጭቆና በመግዛት ብቻ ሳይሆን የማስመስል ሥራዎችን እየሠራ ከብሔራዊ ጥቆሞቻቸው በላይ ለሦስተኛ አገር ሕዝቦች ደንታ የሌላቸውን ኃያላን አገሮች ጭምር በመጠጋትና የነሱን እርዳታም በአገር ስም አላግባብ በመጠቀም ሕዝብ እየመዘበረና የአገርን ብሐራዊ ጥቅም አሳልፎ እየሰጠ አሁንም በጫካ እንዳለ ወንበዴ አገርን የሚያተራምሰው የወያኔ አመራር በጥሩ ምሳሌነት ስለታየ፤ አሁንም ድብቅ ዓላማቸውን ይዘው የጦርነትም ሆነ የተናጥል ፕሮፖጋንዳ የሚነዙ ድርጅቶች መኖር ያስገርማል። ዓላማቸውን ግልጽ ያላደረጉ ድርጅቶችን ዛሬም ሕዝቡ በሞኝነት እንደጎርፍ ወደሚቀይሱለት ቦይ እየጎረፈላቸው የሚከተላቸው ውሀ የሚሆንላቸው አይመስለኝም። በዚሁ መንገድ በሕዝብ ስም ለመጓዝ የሚያቅዱ ቢኖሩ ቆም ብለው ማሰብ ይኖርባቸዋል። ሕዝብ መጋለቢያ ፈረስ አይደለም፤ትግል በሕዝብና ለሕዝብ ዓላማዎች ብቻ መሆን ስላለበት ከሕዝብ የተደበቀ ነገር ሊኖር አይችልም፤ ቢሞከርም ዕድሜ አይኖረውም።

" የትም ፍጭው ዱቀቱን አምጭው " እንደሚባለው ወያኔ ይወገድ እንጅ ማንም ቢተካ ደንታ አይኖረንም የሚለውም አስተሳሰብ ከሞኝነትም አልፎ የተስፋ ቢሶች አቋም ነው። ደርግ እንደዚህ ይጠላ በነበረ ጊዜ ነበር "የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት" / ወያኔ / ስሙን አሻሽሎ ብሐራዊ ቋንቋችንን እየተናገረ የሰላምና ፍትህ ከበሮ እየደለቀ በኢትዮጵያ ላይ ሊነግስና እንደቅኝ ገዥ አገራችንን በብሔር - ብሔረሰብከፋፍሎ በግፍና ጭቆና የወያኔ ሥርወ-መንግሥት /Weyane Dynasty/ ፈጥሮ ከ1983 ዓም ጀምሮ ሊገዛት የቻለው። የብሔር ጭንብል አጥልቀው ሕዝብን ነፃ እናወጣለን የሚሉት ወገኖች በኢትዮጵያ የብሔር እንጂ የመደብ ጭቆና የለም በማለት ከ ፴ ዓመታት በላይ ይህን መስመር ተከትለው ከተጓዙት መካከል የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት አንዱ ስለሆነ ያ ዓላማው በተግባር ላይ ሲውል ምን እንደሆነ እስከሚበቃን አይተናል። ገደል ተጥለው የሞቱ፣ የተረሸኑ፣ በእስር ቤት የሚማቅቁት ሰላማዊ ሰዎች፣ ጋዜጠኞች፣ በጋምቤላ፤ በጉራፈርዳ፣ በምሥራቅ ኢትዮጵያ፤ በጅማ፣ ጎንደር፤ ወዘተና በተለያዩ ኦሮሞ ተናጋሪዎች ውስጥ የትከሰቱት መፈናቀሎች እንዲሁም መሬታቸው ለውጭ አገር ባለሀብቶች የተሸጠባቸው፡ አገራቸው ለባእድ አገር የተሰጠባቸውና በተመሣሣይ ሁኔታዎች በስደት የሚማቅቁት ወጎኖች ምስክሮች ናቸው። ታዲያ ወደዚያ አዘቅት ዳግመኛ ለመውረድ የሚሻ ሕዝብ ያለ የሚመስላቸው ሕዝብን ምን ያህል ቢንቁት ነው ይህን መሰል ዓላማ ለማራመድ የሚሞክሩት ?

የብሔር - ብሔረሰብ ጥያቄዎችን ይዘው አሁንም የሚዳክሩ ወገኖች እንቆምላቸዋለን ለሚሉዋቸው ሕዝቦች የሚበጀውን በዚህ በ፳፩ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ካላወቁ አንድም ምን ጊዜም ማወቅ ስለማይችሉ፤ ወይም አውቀውም መለወጥ ስለማይፈልጉ፤ ሁለተኛም ከቡድን (clique) ወይም ግል ሥልጣን በስተቀር የሚታያቸው ሕዝባዊ ራዕይ ስለሌለ ከዘውድ ተስፈኞች ተለይተው መታየት አይችሉም። የሁለቱም ዋና ዓላማ የማይደፈር የማይገሰስ አምባገነናዊ ኃይል ነውና። የብሔር ጥያቄዎችን አንግበው የሚንገታገቱት ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሥልጣንን ተጋርተው አገርንና መንግሥትን በጋራ ለመምራት ይፈራሉ። ምክንያቱም የተለያዩ ሕዝቦችን እንዲሁም አናሳዎችን ያቀፈ ዲሞክርሲ ሲሰፍን ሕዝቡ ማንን እንደሚመርጥ ስለሚያውቁና ለሥልጣን ዓላማቸው አስተማማኝ ስለማይሆንላቸው ነው። ሐቀኛ የሕዝብ ታጋይ ግን የግል ሥልጣን ራዕይ አይኖርውም። ለእውነተኛ ዲሞክራሲ የሚታገል ሐቀኛ አካል የዚህ ወይም የዚያ ብሔር - ብሔረሰብ ወገንተኛ አይሆንም፡፡ የዲሞክራሲያዊ ትግል ዓላማ የሁሉንም የሕዝብ ክፍሎች ሰብአዊ መብቶች በእኩልነትና በፍትሐዊነት እንደ አንድ ቤተሰብ ልጆች በማየት የሕዝቦችን ትግል በማስተባበር ሕዝቦችን ሁሉ ለሥልጣን ማብቃት ሲሆን በሕዝብ ስም የቡድን /clique/ ሥልጣን ለመፈናጠጥ የሚቃብዙ የፖሊቲካ ሌቦች ይባላሉ፤ ስለሆነም የብሔር-ብሔረሰብ ፖሊቲካ አራማጆች የቡድን ሥልጣን ዓይነተኛ አራማጆች ናቸው።

በዚህ በ ፳፩ኛው መቶ ክፍለዘመን የብሔር - ብሔረሰብ ድንበር የሕዝቦችን ነፃ እንቅሰቃሴና እንደልብ ተደባልቆ የመኖርና መሥራትን፤ ተዛማጅ ባህላዊ እድገትን፤ ልማትን፤ በጋራ ማደግን፣ በነፃ ገበያ ንግድ መጠቀምንና መበልጸግን እንዲሁም አንድ ላይ ሆኖ የፖሊቲካ ኃይል መፍጠርን ይፃረራል። በሌላ አንፃር ተበታትኖ ለገዥዎች መመቸትን ያስከትላል፡፡ ስለዚህ የብሔር

ጭንብል አጥልቀው ሕዝብን ነፃ እናወጣለን የሚሉት ወገኖች ተግባራቸው ሲደመር የሰፊው ሕዝብ ጠሮች ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ ቦልካናይዜሽን የቀድሞዋን ዩጎዝላቪያን እንደ ዳቦ ቆራርሶ እንዳዳከማት ከታሪክ ማወቅ ነበረባቸው፡፡ እንደዚያ ያሉ ታሪኮችን መቅዳት የሚፈልጉ ፀረ-ሕዝብ አምባገነኖች ብቻ ናቸው፡፡

በዘር የተለየ ቡድን ይዞ ለሥልጣን መሮጥ በግለኝነት ላይ ለአተኮረ ጊዜያዊ ጥቅም እንጂ ለዘለቀታዊ የሕዝብ ነፃነትና እድገት የማይጠቅም ስለሆነ ይህን መስመራቸውን ሳይመሽባቸው ቢቀይሩ ይበጃቸዋል። ምክንያቱም ትግላቸው በሕዝቦች መካከል ግጭትንና ጎጂ ቁስል ከመፍጠር በስተቀር ሕዝቦችን ለጋራ ግብ አያቀራርብም፤ አያስተባብርም፤ የፖሊቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት አያመጣም። ለምሳሌ የዚህ የብሔር ወይም ብሔረሰብ አባል የነበሩ መሪዎች እንዲህ ያሉ በደሎችን ስለፈጸሙ ብሔረሰባችን ተበድሎ ነበር በማለት የደረቀውን ጠባሳ ለማደስ የሚያደርጉት ጥረት ከላይ እንደተገለጠው ጊዜ ያለፈበትና ጎታች አስተሳሰብነው።

ይቅር መባባል በመሠረቱ መልካም ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ በመሆኑ የትኛውም ወገን በሌላው ተፎካካሪው ወገን ላይ ያላደረሰው በደል ስለሌለና ከዚህ ጥፋት ነፃ የሚሆን ወገን ስለሌለ ማን ማንን የበለጠ እንደበደለ በእስታቲስቲክስ ማረጋገጥ እስካልተቻለ ድረስ፤ ያውም የጥንት በደለኞችን በዘር አወራርሶ ተጠያቂ ማድረግ ስለማያስኬድና ስለማያዋጣ ያለፈውን ለታሪክ ትምህርት ትቶ ሁኔታዎችን አቻችሉ በማየት ወደፊት ለሕዝቦቻችን በሚበጀው ላይ ከማተኮር የሚሻል ነገር የለም።

በአገራችን ውስጥ በግልጽና በስውር / ተመዝግበውና ሳይመዘገቡ / በሕዝብ ስም የሚንቀሳቀሱ ከመቶ የሚብልጡ ድርጅቶች መኖር የሚያመለክተው ምንድነው ? ወያኔ ከፋፍሎ መግዛት ስለሚሻ በየጎጡ እየተበታተኑ በተለያዩ ቁጥር ድርጅቶቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገለግሉት ያንኑ የወያኔን ዓላማ መሆኑን አለመገንዘባችው አንድም የወያኔ ቀጥታ ወኪሎች ያደርጋቸዋል፤ ወይም አንዳች አውሬ አድኖና በልቶ ከተራረፈው ላይ ለመቀራመት እንደሚያልሙ ቀበሮ መሳይ ተስፈኞች ከመሆን አያልፉም።

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንደሚባለው በትግል ዓለም ላይ እያሉ ከሕዝብ ጋር አብሮ የመሥራት ባህል የሌላቸው፣ በአገር ጉዳይ ላይ ተባብረው የጋራ አቅዋም ወስደው በጋራ የተቀናጀ እርምጃ ያልወሰዱ፣ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን ትተው ሕዝቦችን ለጋራ ዓላማ ለምሳሌ የጋራ ሰላማዊ ሰልፍ አቀነባብረው ከተሞችን በማጥለቅለቅ በወያኔ ላይ ኃይላቸውን ያላሳዩ ድርጅቶች ትክክለኛ ሕዝባዊ ዓላማ ይዘናል ብለው ፀሐፊው እንዳሉት በጠራራ ፀሐይ ተገድለው መስዋዕት የሆኑትን ደጋፊዎቻቸውን በደል ለማጋለጥ ሕዝቡን ለሰላማዊ ሠልፍ አለማስትባበራቸው ምን ያህል ከሕዝቡ ጋር እንደሆኑ ወይም አቅማቸውን ያስገምታል፡፡ እንኳን ባገር ቤትና በነፃው ዓለምም ቢሆን የሕዝብን ቀልብ የሚስብ የጋራ ሥራ ቢሠሩ ሕዝቡ ውስጥ ምን ያህል እንደገቡ ወይም እንዳልገቡ በተረዱት ነበር፡፡ ለሥልጣን ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶችን ለጋራ የሀገራችን ጉዳዮች ለማስተባበር የሚሞክረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎና ሌሎች ሕዝበዊ ድርጅቶች ያዘጋጅዋቸው የመቀራረቢያ የጋራ መድረኮች ጥሩ ምሳሌዎች ሲሆኑ፤ ብዙዎች ድርጅቶች ግን ወደፊትም እንዲህ የሚያደራጃችው አስተባባሪ አካል የሚያስፈልጋቸው ይመስላሉ፡፡ ይህ ታዲያ አንድም የውስጥ ተነሳሽነታቸው ገና ያልበለጸገ ወይም በጋራ በመሥራት ትግላቸውን ያላቀናጁ ስለሆነ በስማቸው ብቻ ወድቆ የሚጠብቃቸው ምንም ነገር አይኖርም።

ፀሐፊው በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጧቸውና የሕዝብ ተከታይም አላቸው ያሏቸው ላይ ሲግልጹ "ሁለተኞቹ ደግሞ ዓለም የምትሽከረከረው በእነሱ ዙሪያ ብቻ የሚመስላቸው ግለሰቦች ሲሆኑ እነሱ ያልመሩት ድርጅት ወይም ትግል ውጤታማ ሲሆን ማየት ሞታቸው ስለሆነ ያንን ለማጨናገፍ የማይገቡበት የለም። " በማለት ገልጸዋቸዋል፡፡

እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች በጋራ የአገር ጉዳይ ላይ ተስማምተው በአንድነት ሕዝቡን እያስተባበሩ ቢሠሩ ወያኔን ለማስወገድ ወደጦር ሜዳ መውጣት ባላሰፈለገም ነበር፡፡ ፀሐፊውም ሲገልጹ ".... የሰላሙ ሁሉ በር ተዘግቶ ወደዚህ አማራጭ ተገደን እየገባን እንደሆነም እንረዳለን" ብለዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ጦርነትን ከነማን ጋር ተዋግቶ ማሸነፍንና ምን ድሎችን ስለማግኘት፤ በጦርነት ድል ቢገኝ ግዳይ ለማን ለማን እንደሚጣል በቅድሚያ ማሰብ ያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ በጦርነት ድል ያገኙ ድርጅቶችን ታሪክ ወደኋላ ዘወር ብለን ስናይ ደግሞ ወይ ከተፎካካሪዎቻቸው ጋር ግንባር ፈጥረው ወይም መጀመሪያ ባላንጣዎቻቸውን በጦር ሜዳ አሸንፈዋቸው ነው በኋላ ድልን ሊጎናጸፉ የቻሉት፡፡ ዶናልድ ሌቪን የተባሉት አሜሪካዊ የታሪክ ፀሐፊ ከተናገሩት ውስጥ ደግሞ የማስታውሰው " እኔ..... አሉ ዶክተሩ..... እኔን የሚያሳዝነኝ በወያኔ ምክንያት የትግራይ ሕዝብ መጠላት ነው፡፡" ሆኖም የጦርነትን አቅጣጫ የመረጡ ወገኖች የቀሩትን ድርጅቶች አሰላልፍ ማጥናት ይኖርባቸዋል፡፡

እነዚህ የተበታተኑ ድርጅቶች መረዳት ያለባቸው ሌላው ነገር እንደ አሜሪካ ያሉ ኃያላን አገሮች ጠንካራ ተቃዋሚ ኃይል መሆናቸውን ካመኑ ትኩረት ሊያደርጉባቸው እንደሚችሉና ደካማ ተቃዋሚዎች ከሆኑ ደግሞ ወያኔ የሚላቸውን ለመቀበል የሚመርጡ መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ ወያኔን የመቀናቀን ኃይል የሌላቸው ወይም የመንግሥት ሥልጣን ለመውሰድ ያልተዘጋጁ ተቃዋሚ ኃይሎች ኃያላን መንግሥታትን የሚያሳስባቸው አይደለም። ኃያላኑ መንግሥታት ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን እስካስጠበቀላቸው ድረስ ጭቆናም ሆነ ዲሞክራሲን ተጠቅሞ በኢትዮጵያ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለውን አመራር እንደሚመርጡ መገንዘብ ይገባቸዋል።

ስለዚህ ዶክተር አሸናፊም ለዘላቂ የሕዝብ ነፃነት የሚበጀውን እያመለከቱ ትምህርትዎን ቢቀጥሉበት፤ ለሎች ምሁራንም እርስበርሳችሁ እየተመካከራችሁ ለነዚህ ለተለያዩ ፖሊቲካ ድርጅቶች ምሁራዊ ምክሮቻችሁን ከመለገስ ባትቆጠቡ መልካም ነው።

ነገር ግን ዛሬም ተበታትናችሁ በየፊናችሁና በብሔር - ብሔረሰብ ተወስናችሁ ለምትዳክሩት ድርጅቶችና  እንደመስቀል ወፍ ብቅ ጥልቅ ከማለት አልፋችሁ በሕዝብ ውስጥ ሕዋሶቻችሁን ዘርግታችሁ ሕዝቦችን ያላቀፋችሁ ድርጅቶች " በትንሹ ያልታመንሽ ........’’ እንደሚባለው ገና በዳዴ ላይ ስለሆናችሁ በአገር ጉዳይ ከሚቀራረቧችሁ ጋር በጋራ በመሥራት በትግሉ ወቅትም ልዩነቶቻችሁን አቻችላችሁ በመተባበርና ሕዝብን በማስተባበር አገራዊ የጋራ የአመራር ባህል ካላሳያችሁን በአገር ጉዳይ ሕዝብን የማስተባበር ወይም የመምራት ብቃት ይኖራችኋል በማለት እንዴት ድጋፍ ልንሰጣችሁ እንችላለን ?

ተፈራ ድንበሩ